EthioLion

# አህያ ፈጅ ቁራ

ከነቅዓ ጥበብ (ለሸርሞ ለሸርሞ ቁ.9 በረከት)

አህዮችን የሚያርድ፣ ሌጦም የሚያወጣ፣
አህያ ፈጅ ቁራ፣ በኢትዮጵያ መጣ።
የአህያ ሥጋ፣ "ካልጋ ሲሉት ካመድ፣"
በዘመነ-ቻይና፣ ታላቅ ታናሽ ሆኖ፣ ጮማው ሲወራረድ፣
እንግዲህ ምን ይላል?! የዘመኑ ትውልድ?!

ያገሬ ባላገር፣ በቆላም በደጋ፣
ኑሮህን ሥትገፋ፣ ሥትኖር በፀጋ፣
ገበያ ስትገበይ፣ ምርትህን ስትጭን፣
አህያ ነበረች፣ ያንተ አጋር እስካሁን።
አሁን ግን ሸክምህን፣ እራስህ ተሸከም፣
በዘመነ-ቻይና፣ አህያ አልተገኘም!
በዘመነ-ቻይና፣ ዘመነ-ጉግማንጉግ!
አህያ ለምግብ፣ ሊታረድ ነው በሕግ!
ጅቦም ጠምህን እደር፣ ቁርጥህን እወቀው፣
ከንግዲህ ጥንብ የለም፣ የቻይና ምግብ ነው!

ምሽ ደስ ይበልሽ፣ በጉግማንጉግ ዘመን፣
ሥጋሽን ለቻይና፣ ቆዳሽን ለጀርመን፣
ተዶልቶብሻል፣ ዶላር ለመተመን።

የሰላም ምልክት፣ አህዮ ደጊቱ፣ ትዕምርተ-ሰላም፣
የተቀመጠብሽ፣ ክርስቶስ በሳሌም፣
ቻይና ሊበላሽ ነው፣ ድምጽሽን አሰሚ፣
ጅቦም እንዲረዳሽ፣ ጠይቂ አታቅማሚ።
የበረሃ እረዳት፣ አልማዝ ባለጭራ፣
በዶላር ወሰደሽ፣ የቻይና አባወራ!

የዘንድሮ ወሬ፣ ሰዶም ወገሞራ፣
በኢትዮጵያ መሬት፣ የአህያ ቁራ?!
እባክህን ጊዜ፣ እግዜአብሔርን ፍራ!

---

ማስታወሻ፡ ኢትዮጵያን ሪፖርተር ላይ "የአህያ ቆዳ በውጭ ንግድ መዝገብ ውስጥ ገባ" በሚል ርዕስ ሥር፤ "*ኩባንያው በወር አራት ሺሕ የአህያ ቆዳ ለመላክ አቅዷል። ከጥቂት ጊዜያት በኋላ የአህያ ሥጋ መላክ ይጀምራል። የቻይና ኩባንያ የሆነው ዶንግ ኢጆ የአህያ ቆዳ እየሰበሰበ ወደ ውጭ ለመላክ የሚያስችለውን ፈቃድ አገኘ፡፡ የአህያ ቆዳ በኢትዮጵያ የወጭ ንግድ ውስጥ ከሚገኙ ዕቃዎች ተርታ በቅርቡ 34ኛ ሆኖ ይመዘገባል፡፡ የሪፖርተር ምንጮች እንደገለጹት፣ የቻይናው ኩባንያ ከአህያ ቆዳ በተጨማሪ የአህያ ሥጋ ወደ ቻይና የመላክ ዕቅድ ነድፏል።* ኩባንያው በመጀመርያው ዙር የወጠነው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አራት ሺሕ የአህያ ቆዳ ወደ ጀርመን ለመላክ ነው፡፡ ...” የሚለውን ዘገባ በዲሴምበር 7፣ 2011 (እ. ኤ. አ.) ካነበብኩ በኋላ የተቋጠሩ ስንኞች።

EthioLion.Com

Ethiopia Will Prevail!